# የኢትዮጵያ ታሪካዊ ቅርሶች በአደጋ ውስጥ ናቸው ተባለ

ኢትዮጵያን በአለም  በታሪክ እና በቅርስ ባለቤትነት ተጠቃሽ ከሆኑት ጥቂት አገሮች መካከል አንዷ እንድትሆን ያደረጓት ታሪካዊ እና ሃይማኖታዊ ቅርሶቿ እጅግ አስጊ በሆነ የመጥፋት አዝማሚያ ውስጥ መሆናቸው ተገለጸ።

የኢትዮጵያ ገዳማት ፣ አድባራት እና የአብነት ት/ቤቶች ( የቆሎ ት/ቤቶች ) ያሉበትን ነባራዊ ሁኔታ በሚል ርዕስ ዙሪያ አጭር ጥናታዊ ጽሑፍ በማድረግ ለግንዛቤ ያህል ለንደን ውስጥ ለሚገኙ በሺዎች ለሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን  አማኞች እና ጥሪ ለተደረገላቸው እንግዶች ባለፈው ሣምንት ገለጻ ያደረጉት እዚሁ እንግሊዝ አገር ውስጥ በተለዋጭ የተፈጥሮ ሃብት ዙሪያ ከፍተኛ ምርምር በማድረግ ላይ የሚገኙት አቶ በላቸው ጨከነ በአሁኑ ወቅት በርካታ አመታት ያስቆጠሩት ሕንፃ አብያተ ክርስቲያናት በእድሳት እጦት ምክንያት በውስጣቸው የሚገኙት ውድ እና ብርቅዬ ቅርሶች መበላሸት ፣ ዘራፊዎች እነዚህ ብርቅዬ እና ውድ የሆኑ ንዋየ ቅድሳት ለመስረቅ ማተኮራቸው ፣ በተለያዩ ጊዜያት በገዳማት እና በዙሪያቸው በሚገኙ ደኖች ላይ የእሳት አደጋ መድረስ እንዲሁም የቆሎ ተማሪዎች እና መምህራኖቻቸው በምግብ እጦት እና በእርዛት ምክንያት ቀያቸውን እየለቀቁ ወደ ከተሞች መሠደድ በታሪካዊ የኢትዮጵያ ቅርሶች ላይ ካነጣጠሩት ዋነኛ ችግሮች የሚጠቀሱ ናቸው ብለዋል።

አቶ በላቸው ከዚህ ጸሐፊ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እነዚህ ታሪካዊ እና ብሔራዊ ቅርሶችን ጠብቆ ለተተኪው ትውልድ ማስረከብ ለአንድ ወገን ብቻ የሚተው ኃላፊነት እንዳልሆነ ይልቁንም አገራችንን ፣ ባህላችን ፣ ቅርሳችንን እንወዳለን የሚሉ ወገኖች በሙሉ በግል ፣ በቤተሰብ እና በቡድን በመሆን በቅርሶች ላይ የተጋረጡትን አደጋዎች ሊታደጉ ይገባቸዋል ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

ይህንን የማሰባሰብ ዘመቻን በተመለከተ በአሜሪካ የሚገኙ የማህበረ ቅዱሳን አባላት እያደረጉት ያለው ጥረትን አቶ በላቸው ሳያመሰግኑ አላለፉም። በተለያዩ ወቅቶች ከኢትዮጵያ በድብቅ መጥተው በእንግሊዝ ፣ በአሜሪካ ፣ በቫቲካን (ኢጣሊያ) . . . ወዘተ በመሳሰሉት ስምንት አገሮች ከሦስት ሺህ በላይ ብርቅዬ የኢትዮጵያ ንዋየ ቅድሳት እና የብራና መጻሕፍት ለባዕዳኑ ሙዚየሞች ከፍተኛ የገቢ ምንጭ ማስገኛ በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ ሲሉ አቶ በላቸው በቁጭት ተናግረዋል። በየአመቱ ኢትዮጵያን ለመጎብኘት ወደ ሃገር ቤት ጎራ ከሚሉት ጎብኚዎች መካከል ከ85% በላይ የሚገመቱት አመጣጣቸው እነዚህኑ በመጥፋት ላይ የሚገኙትን ታሪካዊ ፣ ሃይማኖታዊ እና ብሔራዊ የኢትዮጵያ አሻራዎች የሆኑትን ቅርሶች ለመመልከት ብቻ እንደሆነ በጥናታዊ ጽሑፋቸው ላይ አካተዋል። አቶ በላቸው በቅርቡ ከአማርኛ ወደ እንግሊዝኛ ፣ ፈረንሳይኛ እና ጀርመንኛ የተተረጎመ ዘመናዊ የሕፃናት መማሪያ ዲቪዲ በማዘጋጀት የዜግነት ድርሻቸውን መወጣታቸውን የተለያዩ መገናኛ ብዙኃን ዘግበዋል።

ታምሩ ገዳ (ከለንደን